# የወያኔ ቱሃኖች የሕዝቡን ደም ለመምጠጥ ሲርመሰመሱ

ከተንሳይት በቃና

„ትልቅ አስብ! ትልቅ ታገኛለህ! – (ክፍል ሁለት) „

በአቶ ኤርምያስ ለገሰ በእፕሪል 6 ቀን 2018 ዓ.ም. ከቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚከተሉትን የወያኔ ሆዳሞች ያቀናበሩትን ጸረ-ዶር ዓቢይ ጠቅላይ ሚንስትርነት መረጃዎችን በማቅረብዎ ከልብ ላመሰግን እሻለሁ። ከዚህ በፊት የጻፉትንም አንብቤ በአብዛኛው አስተሳሰብዎ ስስማማ፣ እርስዎ በስም ዝርዝር ያቀረቧቸውን ሰዎች ስለማላቃቸው እዚያ ላይ ምንም ማለት አልችልም።በጣም ከእርሶ ጋር የሚያስማማኝ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አፋጣኝ እርምጃ ወስደው በተለይም የጦር ሃይሉን፣ የደህንነቱን፣ የፖሊሱንና የፋይናንሱን ከወያኔ ሆዳሞችና ወንጀለኞች እጅ በማውጣትና ይህም ተግባራዊ ሆኖ ለሕዝብ የሚታይበት ሁኔታ ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ሌሎቹ እርምጃዎች ሁሉ ተፈጻሚነታቸው አጠራጣሪ ይሆናል። እርሶም በዚህ ጽሁፍዎ የወያኔን ወንጀለኞችና ሆዳሞች ጸረ-አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር የራሳቸውን ወጥመድ በማዘጋጀት ራሳቸውን ለማዳን እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ አቅርበዋል። እንደ በረከት ስምዖን፣ እንደ አባ ዱላ ገመዳ፣ እንደ ሽጉጤና እንደ አባይ ጸሐይ ዓይነቶቹ የታሪክ አተላዎችና ወንጀለኞች መሰረታዊ ለውጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመጣ ፍጹም ፍላጎታቸው ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እስካሁን ለተፈጸሙት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችና ግድያዎች ሙሉ በሙሉ ተጠያቂዎች ናቸው። ዓላማቸው አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ዶር ዓቢይን በተዘዋዋሪ ስልጣኑን በሚፈለገው መልኩ የሚጠቀመበትን ሁኔታ ለማኮላሸትና በወያኔ ቧንቧ እንዲፈስ ለማስገደድ የተጠነሰሰ ሴራ ነው። ወያኔና የወያኔ ሆዳሞች የአሻጥሮች ጥንሰሳ አቶ ኤርምያስ በጽሁፋቸው ውስጥ በሚከተለው መልኩ አቅርበውታል። „ ከውስጥ የሚወጡ መረጃዎች እየሰማን ያለነው ነገር በጣም አስደንጋጭ ነው። አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ከጨዋታ ውጪ የሚያወጣ ኢመደበኛ አደረጃጀቶች የወሳኝ ስራዎች ባለቤት ሆነዋል። መጀመሪያ በ12 የተደራጁ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በኃላ ወደ 7 የወረዱ ግብረ ሃይሎች ( Task Force) ተደራጅተው የጠቅላዩን ወሳኝ ስራዎች ጠቅልለው ወስደዋል። ከሁሉም በላይ ለውጥ ይመጣል በሚል ተስፋ ላደረጉ ኢትዮጲያውያን የሚያሳዝነው ክላስተሩን የሚመሩት ሰዎች እነማን እንደሆኑ መታወቃቸው ነው። ቡድኑ እስከሚቀጥለው የኢህአዴግ ጉባኤ ይቀጥላል መባሉ ሌላ አስደንጋጭ መርዶ ነው። ቢያንስ አራቱን እንመልከት። # የመጀመሪያው ግብረ ሀይል " ዲሞክራታይዜሽን" የተባለ ስያሜ የተሰጠው ሲሆን የክላስተሩ አስተባባሪ በረኸት ስምኦን እና ህላዌ ዩሴፍ ናቸው። በረኸት በመላው ኢትዮጲያ ያሉ የህዝብ አደረጃጀቶችን፣ ሲቪክ ማህበራትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ወጣቶችና ሴቶችን በሀላፊነት እንዲመራ ተሰጥቶታል። በሌላ አነጋገር የኢህአዴግ ቢሮን፣ የወጣቶች ሚኒስትርን፣ ሴቶች ሚኒስትርን፣ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርን በክላስተር የሚመራው በሕዝብ እጅግ የሚጠላው በረኸት ስምኦን ሆኗል። በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ቦታዎች የሚካሄዱ የህዝብ ስብሰባዎች ሰነድ የሚዘጋጀው፣ መድረክ መሪ የሚመርጠው፣ በየቀኑ የመወያያ ነጥቦች የሚያሰራጨው እና የሚመራው በረኸት ስምኦን ነው። ከዚህ በተጨማሪም " ምድር አንቀጥቅጥ" የሚል ስያሜዎች የተሰጣቸውን ስብሰባዎች እየገመገመ በድርጅት እና የመንግስት ሚዲያዎች እንዲተላለፉ፣ ተሳታፊዎችን ወደ ፓርቲ ምልመላ መምጣታቸውን የሚያረጋግጠው ህላዌ ዩሴፍ እንደሆነ ተነግሮኛል። በረኸት፣ ህላዌና ሽፈራው ሽጉጤ ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር እሳትና ጭድ መሆናቸው ለሚያውቅ ደግሞ ዶክተር አቢይ የገባበትን አጣብቂኝ በቀላሉ ይገነዘባል። # ሁለተኛው ክላስተር " የኢኮኖሚ ጉዳዬች ግብረ ሀይል" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ክላስተሩን የሚመሩት ህውሓቶቹ አርከበ እቁባይ እና ዶክተር አብርሃም ናቸው። # ሶስተኛው ክላስተር " ድርጅት የማጠናከር" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ፓርላማውን፣ የክልል ምክር ቤቶችን፣ የማእከላዊ ኮሚቴ እና እስከ ቀበሌ ያለውን ምክር ቤት የሚመራ ነው። ለዚህ ክላስተር ሃላፊነት የተሰጠው በዋናነት

ለአባዱላ ገመዳ እና ሽፈራው ሽጉጤ ነው። ከዚህ በኃላ ከላይ እስከ ቀበሌ ያሉት የምክር ቤት አባላት ወደ ድሮ አድርባይነታቸው እንዲመለሱ ለአባዱላ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል። # ሌላው አስቂኝ ግብረ ሃይል " ህገ ወጥነት መከላከል" የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን የበላይ አስተባባሪው አባይ ፀሀዬ መሆኑ እየተገለጠ ነው። # ሌላው ክላስተር " የውጭ ግንኙነት" የሚባል ሲሆን አስተባባሪው ስዩም መስፍንና ወርቅነህ ገበየሁ ናቸው። ይሄ ቡድን የውጭ አገሮችን ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጲያውያንን እና ትውልድ ኢትዮጲያውያንን የማማለል ስራ ይሰራል። በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ አንዳንድ ግለሰቦች በዲያስፓራው ስም እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ ከጀርባ ሆኖ የሚመራው ይሄ ቡድን እንደሆነ ይነገራል። ማ ስ ጠ ን ቀ ቂ ያ:- መልእክቱን ያደረሱን ሰዎች ዶክተር አቢይ በአንድ ሳምንት ውስጥ ይሄንን በግብረ ሃይል ስም በጓሮ በር የገባውን ክላስተር ማፍረስ ካልቻለ በመጀመሪያው ወራት ኃይለማርያም የገባበትን ቅርቃር ስተት ብሎ ይገባል። እናም ጊዜ ሳያጠፋ በይፋ ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ክላስተሮቹን ማፍረስ ይኖርበታል። አባይ ፀሀዬን፣ በረከትን፣ ስዩም መስፍንን፣ አርከበ እቁባይን በጡረታ መሸኘት አለበት።" „የካቢኔ ለውጥ ይኖራል ወይ? የካቢኔ ለውጥ ይኑር አይኑር የሚለው አጀንዳ አዲስ መጨቃጨቂያ ሆኖ ብቅ ብሏል። ህውሓቶች ባጠቃላይ፣ ብአዴን ውስጥ የበረከት ኔትወርክና የሽፈራው ሽጉጤ ክሊኮች በአንድ መስመር ተሰልፈዋል። እነዚህ ሀይሎች ክፍተት የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ በመሆኑ አዲስ ካቢኔ መኖር የለበትም የሚል አቋም ወስደዋል። ህወሓት በደብረጽዮን ምትክ ከህወሓት ስራ አስፈፃሚ ይመድባል በሚል ግልፅ አድርገዋል። ከላይ የተጠቀሱት ሕወሓቶችና ተላላኪዎቻቸው የያዙት አቋም " አዲስ ካቢኔ የሚደራጅ ከሆነ እንኳን ስልጣኑ የብሔራዊ እና ኢጋር ድርጅቶቹ ነው" የሚል ነው።የጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን የሰጠነውን ተቀብሎ ስምሪት መስጠት ብቻ ነው እስከ ማለት ደርሰዋል። በተለይ በበረኸት የሚመራው ብአዴን ከህወሓት በላይ ህወሓት የሆኑትን ጌታቸው አምባዬ፣ ከበደ ጫኔ፣ አለምነው መኮንን፣ ዶክተር ጥላዬ ጌቴ፣ አቶ አህመድ አብተውን ለሚኒስትርነት በፊት መስመር አሰልፏል። ሽፈራው ሽጉጤም ራሱን ጨምሮ ከዶክተር አቢይ ጋር አይንና ናጫ የሆኑትን ሲራጅ ፈርጌሳ፣ ሞፈሪያት ካሚል፣ ተስፋዬ በጅጋ፣አሰፋ አቢዩና ተክለ ወልድን ማሰለፋ እየተነገረ ነው። መጨረሻው ምን ይሆናል? ከዶክተር አቢይ አቅም በላይ ነው? በፍፁም! የማያቋርጥ የህዝብ ትግል እስከቀጠለ ድረስ! በተጨማሪም ትልቅ የሚያስብ በመሆኑ?" የሚል ጠቃሚ መረጃዎችን አቅርበዋል። ለእኔ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ብአዴንና ኦህዴድን ከሆዳሞቹ ከእነ በረከትና አባ ዱላ ገመዳ እጅ ወጥተው ተባብረው ሃይል ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ እውን ማድረግ ካልቻሉ፣ የወያኔ ሆዳሞች ጠቅላይ ሚኒስትሩን በቀላሉ ሊያስወግዱ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊፈጥሩ ይችላሉ።የቄሮ፣ የፋኖና መርዛና የህዝቡ ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ይመስለኛል። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ግፈኛው የወያኔ መንግስትና የእሱ ጥቅም ተካፋዮች ወያኔ ያልሆኑት የአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ያሉት በአንድ ወገን ሲሆኑ፣ በሌላው ወገን ግፉ፣ ግድያውና መሰቃየቱ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የወጣቱ ትውልድ መብቱን ለማስከበር እየታገለ የሚገኝበት ነው።መፍትሄውም ያለውን ግፈኛ የወያኔ መንግስት ከእነ ግብረ አበሮቹ ማስወገድና ሌላ ሕዝቡ በሚፈልገው መልኩ አንድ ዴሞክራቲክ የሆነች ኢትዮጵያን የሁሉም መብት የሚከበርባት፣ ጥቂቶች የማይፈነጩባት አስተዳደር እውን ማድረግ ነው።

ከተንሳይት በቃና

7.4.2018